# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"…እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ::" ኢሳ 48÷17

God's Love, P.O.Box 6734, L.S. MO 64064.
E-mail mtizazu@hotmail.com -Fax/Ph 816 – 246-9395

ሐምሌ 1994 JULY 2002

አዘጋጅ:- መላኩ ትዕዛዙ

**"ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ÷ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል::" ት/ኢሳይያስ 54÷13**





# "አንድ ይሆናሉ"

"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል÷ በሚስቱም ይጣበቃል፤ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ::"(ኦሪት ዘፍጠረት ምዕራፍ 2 ÷ 24)

*በዚህ ዘመን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገደው ሁሉ ስለ ትዳርም ይገደዋል:: ምክንያቱም የሰው ልጆች ጠላት የሆነው ሴይጣን:- ከሁሉ ይልቅ የሚቃወማቸው÷ ቢቻለውም የሚያጠፋቸው እግዚአብሔር ለሰው ከፈጠራቸው ዋና ተቋሞች አንዱ ትዳር ስለ ሆነ ነው:: ሌላኛዋ ቀንደኛ የሴይጣን ጠላት ቤተ ክርስቲያን ናት::*

*ትዳር ሰው ፍቅርን የሚማርበትና የሚለማመድበት ዘሩን የሚያበዛበት÷የሚያርፍበትና እግዚአብሔርን የሚያመልክበት÷የተፈጠረበትንም ዓላማ እንዲፈጽም የሚረዳው ቅዱስ ተቋም ነው::ሴይጣን ትዳርን ተግቶ የሚዋጋው ለዚህ ነው:: ስለዚህ ትዳሩን በቸልታ የሚመለከት ሰው በራሱና በአምላኩ፡ በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ ታላቅ በደልን ያደርጋል:: የሚከተለው የአንባቢዎቻችንን ልብ በትዳር አኳያ ለማነቃቃት የቀረበ ነው::* (ትዳርን ቀና ለማድረግ የሚረዳ ጥበብ) *በሚል ርዕስ ላራ ሒንተን የምትባል የእግዚአብሔር ሰው ከጻፈችው ተወስዶ የተዘጋጀ ምክር ነው::)*

ትዳር በመጀመርያ ደረጃ በፍቅርና ለፍቅር ተብሎ መጀመር ይገባዋል:: ፍቅርም ነፍስ እንዳለው ነገር ታዳጊ መሆኑን በማወቅ:- ባለትዳሮች ሁልጊዜ ፍጹም ወደ ሆነ አንድነት ማደግን ዓላማቸው ማድረግ ያስፈልጋቸዋል:: በዘፍጥረት 2÷24 "ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል÷ በሚስቱም ይጣበቃል ፡ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ::" የሚለው ቅዱስ ቃል÷ የትዳር ሁሉ ዓላማ ነው:: ይህም "አንድ ይሆናሉ" የሚለው ቃል ወደ ፊት የመቀጠልን ሁኔታ የሚያመለክት ስለሆነ ነው፡ትዳር ታዳጊ ነው ያልነው:: በመሆኑም ጥሩ ትዳር ያላቸው:- የተሻለ እንዲኖራቸው÷ ሰላም የሌላቸው ደግሞ ወደ ፍቅርና መደጋገፍ እንዲያድጉ የጌታ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው::

(የሚከተሉት ሃሳቦች ማንንም ሳያስቀይሙ የፈጠራ ችሎታን ለመቀስቀስ የተመረጡ እንጂ ፎርሙላዎች አይደሉም::)

እንግዲህ ትዳር ታዳጊ ነው ካልን ታዳጊ ነገሮች ሁሉ ምግብ ያሻቸዋል ወደሚለው እውቅ ድምዳሜ እንደርሳለን፤ የትዳር ማዳበሪያው ከልብ መተዛዘንና ርኅራሔ ነው:: ስለዚህ:- ትንሽ ትንሽ ከጊዜህ÷ትንሽ ትንሽ ከጉልበትህ÷ፍሬ በመጠባበቅ ዘርን እንደሚዘራ ገበሬ በትዳር ጓደኛህ ላይ ዝራ:: የባለቤትህን ልብ ለመባረክ (ደስ ለማሰኘት) የሚያስፈልገው ብዙ ነገር አይደለም:: ነገር ግን ከዕውነተኛ አሳቢነት የመነጩ የየዕለቱ ትናንሽ ተስፋዎች ልብን ያሳርፋሉ:: ያረፈች ነፍስ ደግሞ ለሰላም ትመቻለች:: ባለቤቴ አለልኝ የሚል ዕምነትና ተስፋ ክፉ የተባለውን ሰው እንኳ ገራምና ምቹ ያደርገዋል:: ስለዚህ በአንተና በባለቤትህ መካከል ፍቅርን ለማሳደግ የደግነትንና የርኅራሔን ማዳበሪያ ጨምርበት:: አብዛኛው ሰው ለባለቤቱ የማይራራው በክፋት አይደለም:: በአንዱ ወይም በሁለቱም ኣለማስተዋል ነው:: ስለዚህ እንንቃና እናስተውል!! ለሰላማዊ ሕይወትም እንነሣ!!

የሚከተሉት ለትዳር ጓደኛህ ትልቅ ትርጉም የሚሰጡ ከባድ ያልሆኑ÷ የደግነት (የፍቅር) ተግባሮች ናቸው:-

- የሚቻለውን ያህል ቋሚ የጋራ የፀሎት ጊዜ ይኑራችሁ :-
- በሚገባት መንገድ ከልብ እወድሻለሁ በላት :-
- በየጊዜው የሚቻልህን ልዩ ምግብ አዘጋጅተህ ሁለታችሁ በደስታ አኳኋን ተመገቡ :-
- ስለ ሁለታችሁም ሕልምና ራዕይ ÷ ምኞትና ፍላጎት በመግላለጽ ተነጋገሩ (በዚህም አንዱ የሌላውን ፍላጎት በራስ ወዳድነት አይቃወም፤ይልቁን አንዱ ለሌላው ምኞት መከናወን መንገድ ይፈልግ) :-
- ለባለቤትህ ያልታሰበ ስጦታ መስጠት ልመድ (ውድ ነገር መሆን የለበትም) :- አንዱም የሌላውን ስጦታ ከልብ ያድንቅ::
- በሰዎች ፊት ስለ ባለቤትህ መልካም ነገር ተናገር፡
- ባለቤትህ ስትናገር ለመልስ ሳትቸኩል ወይም ሳታቋርጥ ልብ አድርገህ አዳምጥ::
- ሰላምንና ደስታን የሚፈልግ ስለሚያገኛቸው የሚያስቅ ነገር ፈልጋችሁ አብራችሁ ተጫወቱና ሳቁ፡
- ከባለትዳሮች ወዳጆቻችሁ ጋር ለመገናኘትና አብሮ እንጀራን ለመቁረስ አትስነፉ:-
- ውሳኔዎች ከማድረግ በፊት አስቀድማችሁ ተነጋገሩ÷ ይህ በጉዳዩ ላይ ለመተባበር ይረዳል::
- ሆን ብላችሁ መመስጋገንን አዘውትሩ :-
- በየዕለቱ አለመግባባታችሁን ሳትፈቱ ወደ መኝታችሁ አትሂዱ:- የሰላም መንፈስ በጋራ ይጠበቅ!
- ሁለታችሁ በጋራ የምትወዱትን ነገር ቢያንስ ለአንድ ሰዓት በየሳምንቱ አብራችሁ አድርጉ "አብሮ የሚፀልይና አብሮ የሚጫወት ቤተሰብ አብሮ ይቆያል" ("A family that prays together and plays together, stays togather")

የሚከተለውን የእግዚአብሔር ቃል ከትዳር ሆነ ከማንኛውም የሰው ልጆች ኑሮ አኳያ ማሰላሰል እጅግ ይጠቅማል::

*"ፍቅር ይታገሳል፥ቸርነትንም ያደርጋል፡ ፍቅር አይቀናም ፍቅር አይመካም፥አይታበይም፥የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም ከዕውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመፃ ደስ አይለውም ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።" (1ቆሮንጦስ 13፥4-7) በእግዚአብሔር ቃል ትምሕርትና ለመንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ እጅግ የተባ ሸና የደረቀ ሕይወት ለምልሞ ሲያምር ብዙ ጊዜ ታይቷል፤ ዕረፍት ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይጀምራልና "የሚሰማ ጆሮ ያለው ...ይስማ" እንደተባለው፡- ለቃሉና ለመንፈሱ እንታዘዝ። አይዞህ!! አይዞሽ!!*

---

# የፀሎት ጓደኛ

ነፍስ ወከፍ የግል ፀሎት በምንም የማይተካ የቅዱሳን ሕይወት ማዕከላዊ ባሕርይ ነው። ይሁን እንጂ ከሌሎች ጋር በፀሎት መተባበር የዚያኑ ያክል የእግዚአብሔር ፈቃድና አስፈላጊ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሚከተለው ያረጋግጥልናል። *"ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያ ት ካለው አባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆ ናለሁና።"* (የማቴዎስ ወንጌል 18፥ 19-20)

### የሕብረት ፀሎት ጥቅሞች ፡-

*ኃላፊነት እንዲሰማ ይረዳል። በኑሮ ጫና እና በጣላት ውግያ ብዛት የተናጥል ፀሎት ከሕብረት ፀሎት ይበልጥ ሊዳከም ወይም ሊሰተጓጐል ይችላል። ከፀሎት ጓደኛ ጋር የተወሰነ የፀሎት ቀጠሮ ካለ ግን ለማስተጓጐል ቀላ ል አይሆንም። ድካምንና ስንፍናን ለመቋቋም ይረዳል። በተጨማሪም ከፀሎት ጓደኛ ጋር በመመካከር ወደ ፀሎ ት ስንቀርብ በፀሎታችን ዓላማ ላይ ማተኮር ይቀላል።

*ወዳጅነትን ያጠብቃል። በዚህ ዘመን በክርስተያንም መካከል እንኳ የጠበቀ ታማኝ ወዳጅነትን መፍጠርና ማቆየት ከባድ እየሆነ የመጣ ይመስላል። በተለይም በእንዱስትሪያዊው ሐገሮች፥ መገናኘት እንኳን ዕሑድ በአምልኮ ሥፍራ ብቻ እየተወሰነ ሲሄድ ይታያል። ሁሉም በየቤቱ ለየብቻው የሚቃተትበት ዘመን ይመስ ላል። ሴይጣን ይህን ሁኔታ ተቀብለን ዝም ብንል ደስ ታውን አይችለውም። ለየብቻ የምንመቸው ለእግዚአ ብሔር ሳይሆን ለእርሱ ነውና። በቅርቡ (በዚህ በአሜ ሪካ) midwest ራሷን ሰቅላ ለመሞት የመረጠችው እህት ልቧን ከሽንፈት የሚመልስ የልብ ጓደኛ ነበራት አንል ም። የፀሎት ጓደኛ ዕውነተኛ የክፉ ቀን ደራሽና ደገፋ ነውና። ከዚህም በላይ፡- በሕብረት ፀሎት ውስጥ፥ አን ዱ የሌላውን ሸክም ይሸከማል። በልብ ስብራት፥ በመ ከራ ወይም በሀዘን ጊዜ አንዱ ለሌላው የፀሎት ደጋፊ ብቻ ሳይሆን አጽናኝና መካሪም ይሆናል።

*ፍቅርን ለመማርና ለመለማመድ ዕድል ይሰጣል። አዎን፥ፍቅርን ይማሩታል። ከእግዚአብሔር ቃል፥ከ መጽሐፍ ቅዱስ ይማሩታል። እንደ እርሱ ያለ ዕሙን የፍቅርና የዕውነት አስተማሪ ስለማይገኝ፡- ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፉው ሰው ደግና አፍቃሪ ይሆናል። "ል ጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፤ የል ጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።" ተብሎ እንደ ተጻፈ። እንግዲህ የእግዚአብሔር ሰው ከቃሉ የተማረውን ዕውነት፡- ፍቅርንና ፈርሐ እግዚአብሔርን ለመለማመ ድ ከፀሎት ጓደኛው ይልቅ የሚያመቸው አያገኝም።...

ምክንያቱም አዘውትሮ በጌታ ፊት ተስማምቶ በፀሎት የመቅ ረብ መንፈሳዊ አንድነት፡- ጓደኝነትን በቅድስና ስለሚሞላው ነው። መልካም የፀሎት ጓደኝነት ባለበት፡-መተሳሰብ፥መደጋ ገፍ፥ መተራረም፥ፀሎት ሲመለስ አብሮ መደሰት፥መጽናናት እና አብሮ እንጀራ መቁረስ ስለሚኖር ዕውነተኛና ቅዱስ ጓደኝነት የማይቀር ነው።

## የፀሎት ጓደኛ አመራረጥ፡-

ጊዜ ወስዶ በፀሎት የእግዚአብሔርን ምሪት መፈለግ፥መጠበቅና መከተ ል ያስፈልጋል። የሚከተሉትን ባሕሪያት ይኑረው፡-

*ሚስጢረኛነት ፡- የእግዚአብሔር ሰው በአምላኩ ፊት የሚያለቅስበት የተለያዩ ሚስጢሮች ይኖሩታል። በድፍረት ሆነ በስሕተት የተፈጸሙ በደሎችን መናዘዝ ይኖራል። እነዚ ህም ኑዛዜዎችና ንስሐዎች በሚስጢር መያዝ ይኖርባቸዋል። የወንድማማች ሚስጢር መጠበቅ መተማመንን፥ይህም ንፁሕ ፍቅርን ሲያስከትል፡- ፍቅር ባለበት መስማማት ይኖራል። በመስማማት የተደረገ ፀሎት ደግሞ መልስ እንዲያገኝ በቃሉ የታዘዘ ነው። ስለዚህ ፍጹም ሰው ባይኖርም እንኳ የፀሎት ጓደኛ ሲመረጥ በዚህ አኳያ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

*በተቻለ መጠን ጽኑ መንፈሳዊ መሠረት ያለው ይሁን። ይህም የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅና በሕይወት በሳልነት ነው። በተጨማሪ መንፈሳዊ ጓደኝነት መስመር ለቅቆ ወደ ሥጋዊ የሀሜትና የወሬ ግንኙነት እንዳይለወጥ፥ ከምርጫው ጀምሮ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

*የንስሐና የቅድስና ሕይወት ይኑረው። ሳይናዘዙና ይቅር ታ ሳይቀበሉ በኃጢአት የሚደረግ ፀሎት ወደ ጌታ ስለማይ ደርስ፥ የንስሐ ሕይወት እጅግ አስፈላጊ ነው።

*ኃጢአተኞችን (እግዚአብሔርን የማይፈሩትን) "መስሎ አዳሪ" አይሁን። በፀሎትና በጾም ሕይወት ለማደግ ዋጋ ስለ ሚያስከፍል ቆራጥ ፈቃደኝነት ያስፈልጋል። ስለ መቀራረብ ብዛት፡- አንድ ወንድ ከአንድ ሴት ባይሆን ይመረጣል።

በመጨረሻም፡- ለዚህ የሚመቹህን ሁለት ወይም ሦስት ሰ ዎች ከአሁኑ በማሰብ ጹምና ፀልይ። እነርሱም በሀሳብህ ከተ ስማሙ በጾም-ፀሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈልጉ አ ሳስባቸው። አንተም በዕምነትና፥በቅንነት ልብህን አዘጋጅ። ጌታም ፍሬ የበዛላችሁ ደቀ መዛሙርት ሊያደርጋችሁ ፈጥኖ ፀሎታችሁን ይመልሳል። እግዚአብሔር ይመስገን።

---

**ምስጋና ፡-** በኦቨርላንድ ፓርክ (ካንሳስ) የምትገኘው አማኑኤል የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን በቋሚነት ል ትረዳን በመወሰኗ የተሰማንን አድናቆትና ደስታ ከምስጋና ጋር እንገልጻለን። ጌታ በብዙ ፍሬ ይባረካችሁ።

---

ወንድም ስንታየሁ አረዶ (ከሕውስተን ቴክሰስ) የላክህልን ቸር ስጦታ ደርሶናል። ወንድማችን፥አብረን የምናገለግለ ውና የምንተጋለት ንጉሡ ኢየሱስ በክብሩ ሲገለጥ አብሮት የሚገለጠውን ዋጋችንን ዓይን አላየችውም፥ ጆሮም አልሰ ማውም። ጌታ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክህ።

---

በኢትዮጵያ፥በኬኒያ፥በሱዳን፥በጂቡቲና በመሳሰሉት ሐገሮ ች ለሚኖሩ ወገኖች መልዕታችንን እንድንልክ የምታውቋ ቸውን አድራሻዎች ላኩልን። የፖስታ ዋጋውን አክላችሁ መላክ ባትችሉም እንኳ አድራሻዎችን ላኩልን።

---

ፀልዩልን! ኢየሱስ ጌታ ነው። ጌታ ይባርካችሁ። መላኩ ትዕዛዙ